# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

***መስከረም 19 ቀን 2005 ዓ.ም.***

### በጎንደር ወያኔና ህዝቡ ከባድ ግጭት ውስጥ ገቡ ፤

### ከ70 በላይ ሰዎች በጥይት ተመቱ፤

### የኦህዴድ አፍለኛ ካድሬዎች ጥያቄ ወያኔን አስደንግጦዋል፤

የወያኔ ቡድን በአዲሱ ዓመት አዲስ የጥቃት ዘመቻ ከፍቶ የጎንደርን ህዝብ በመሳሪያ እያሳደደ ሲጨፈጭፍ መክረሙን ከጎንደር እስቲ መካነ እየሱስ ከተማ የደረሰን ጥቆማ ገለፀ።

ለቀናት በወረዳው የመንግስት ሰራተኞች እና የግል ድርጅት ተቀጣሪዎች እንዲሁም በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ የከተማዋ ነዋሪዎች የስራ ማቆም አድማ አድርገው የሰነበቱ ሲሆን ሰኞ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም ወያኔ ባዘመተው የክልሉ ልዩ ኃይል እና የፌዴራል ፖሊስ አማካኝነት በህዝቡ ላይ የእሩምታ ተኩስ ከፍቶ ከ70 በላይ ሰዎች ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል።

ከሶስት ዓመት በፊት የእስቲ መካነ እየሱስ ከተማን ከጎንደር እና ከደብረ ታቦር እንዲሁም ከሞጣ ከተሞች ጋር ለማገናኘት የሚያስችል የመንገድ ስራ ጥናት ተደርጎ በጀትም ተመድቦ ለህዝቡ ይፋ ተደርጎ ስራው ይጀመራል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ የተጠናቀቀው ጥናት ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ተሰርዞ አዲስ የመንገድ ጥናት በሚል ቀድሞ የነበረው በመሰረዙ የተበሳጩ የወረዳው የመንግስት ሰራተኞች ለአንድ ሳምንት የስራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውን ተከትሎ የአካባቢው ህዝብም ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስተጋባ የሰነበተ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

ህዝቡን ደብቀው በምስጢር አዲሱን የመንገድ ስራ ለማስጀመር ከኮንራክተር ድርጅቱ አመራር ጋር የዞኑ ባለስልጣናት ድል ባለ ግብዣ ጎንደር ከተማ መፈራረማቸውን የሰሙ የወረዳው ነዋሪዎች ሰላማዊ በሆነ መልኩ ቀድሞ የነበረው ጥናት ተግባራዊ ይሁን በማለት ጥያቄ ቢያቀርቡም ሰሚ አና አድማጭ በማጣታቸው በአደባባይ ተቃውሞ ከአንዴም ሁለቲ ሲያስተጋቡ እንደነበርና በቅርቡም

ምላሽ እንደሚሰጣቸው የወረዳው አስተዳዳሪን ጨምሮ ሌሎች ስራ አስፈጻሚዎች የገለጹ ቢሆንም በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ እዘዝ ዋሴ በተባለው ግለሰብ አሻፈረኝ ባይነት የህዝቡ ጥያቄ ውድቅ በመደረጉ ባነሱት ተቃውሞ ሰኞ ዕለት በፌዴራል ፖሊስ እና በክልሉ ልዩ ኃይል በተወሰደ እርምጃ ብዙ ሰዎች በጥይት ሲመቱ ......አባት እና ልጅ ወደ ዱር ሲሰደዱ..... እናት ደግሞ ለእስር መዳረግዋንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልጾዋል::

በተለይ ሰኞ መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም በከተማዋ የሳምንቱ ታላቅ ገበያ የሚከናወንበት ዕለት መሆኑ እየታወቀ ከጎንደር የመጣው የፌዴራል ፖሊስ እና ልዩ ኃይል ድንገት በከፈተው ተኩስ በከተማዋ ነዋሪዎች እና ለገበያ በመጣው የገጠር ህዝብ ላይ ከባድ ጉዳት ከማድረሱም በተጨማሪ ሴቶችን እያፈሱ ወዳልታወቀ ሰፍራ ሲያጉዋጉዛቸው ወንዶቹ በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ጫካ ሊሰደዱ እንደቻሉም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

ድንገት በተከፈተው ተኩስ የተደናገጡ ህጻናት ከወላጆቻቸው ተለያይተው መድረሻ አጥተው ከወዲያ ወዲህ እያሉ ሲያለቅሱ ለተመለከተ ሰው እጅግ አንጀት የሚበላ እንደነበር የገለፀው የደረሰን ዘገባ ወያኔ በሀውዜን ህዝብ ላይ ደርግ ፈጸመ ብሎ ካሳየው የአውሮፕላን ጭፍጨፋ ፍጹም ያልተለየ እንደነበር ይሄው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያችን ይመለስልን ብለው ባዶ እጃቸውን ለተቃውሞ ወደ አደባባይ በወጡ የእስቲ መካነ እየሱስ ከተማ ነዋሪዎች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል ዘግናኝ ጭፍጨፋ ሲደረግ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ እዘዝ ዋሴ የተባለው ግለሰብ በፌዴራል ፖሊስ ታጅቦ በከተማዋ እየተዘዋወረ ሴቶችንና ህጻናትን እያፈሰ በጭነት መኪና ወዳልታወቀ ስፍራ ሲያስግዝ እንደዋለም ታይቶዋል::

ከተማዋን መሀል ለመሀል አቋርጦ ሊገነባ የነበረው አስቀድሞ የነበረውን የመንገድ ጥናት ወደ ጎን በማድረግ አዲስ ጥናት በሚል የመንገድ ስራው አቅጣጫውን ቀይሮ እንዲሰራ የክልሉ ፕሬዝዳንት አያሌው ጎበዜና የዞኑ አስተዳዳሪ እዘዝ ዋሴ የተባሉት በምስጢር ከተቋዋራጭ ድርጅቱ አመራር ጋር በመመሳጠር ህዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም ስራው እንዲጀመር የተፈራረሙ መሆኑን ያወቀው የወረዳው ህዝብ ቁጣውን በተቃውሞ መልክ በመግለጹና ምስጢሩን በማጋለጡ የተበሳጩት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት በወሰዱት የጥፋት እርምጃ በርካታ ሰዎች ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በህክምና ማዕከል ተኝተው የሚገኙ ሲሆን በተለይ በከተማዋ ውስጥ ታዋቂ ሆቲል ባለቤት የሆነች አንዲት ሴት በጥይት ሆድዋን ተመትታ አንጀትዋ ወጥቶ መሬት ለመሬት ስትጎተት እንደነበር የአይን እማኞች ጥቆማ አጋልጦዋል::

ይህን የመሰለ ዘግናኝ እርምጃ በህዝቡ ላይ የወሰዱት የወያኔ ባለስልጣናት በድርጊታቸው ከመደንገጥ ይልቅ በኩራት ሽፍቶችን ስትቀልብ የነበረች ናት እያሉ መናገራቸው እጅግ አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን አሳዛኝ ነው ያሉት የአካባቢው የአይን እማኞች ወደ ጫካ የገቡት የከተማዋ ወጣቶች በአሁኑ ወቅት የት እንዳሉ የማይታወቅ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

ሰሞኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የብአዴን ሊቀመንበር ደመቀ መኮንን የተባለው ባለስልጣን ከዚህ ቀደም ከጎንደር ለም መሬት ተቆርሶ ለሱዳን በተሰጠ ግዜ ህዝቡ

አምጾ ተቃውሞ በማሰማቱ የፌዴራል ፖሊስ እና የመከላከያ ሰራዊት  በህዝቡ ላይ የእሩምታ ተኩስ ከፍቶ እልቂት እንዲፈጠር ያደረገ ሲሆን አሁንም በእሱ አምሳያ የተፈጠሩት እነዚሁ የወያኔ ግልገል ባለስልጣናት በህዝቡ ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ እየፈጸሙ መሆኑ አስገራሚ ነው ተብሎዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኩርፊያ ማዕበል እየተናጠ የሚገኘው ኦህዴድ አሁንም ባለስልጣናቱ ውስጥ ውስጡን የእርስ በርስ ንትርክ እያደረጉ ነባሩና አፍለኛው ቡድን ለይቶ እየተወዛገቡ መሆኑ ተሰማ፡፡

በቅርቡ በተደረገው የጠቅላይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት ላይ ኦህዴድ የራሱን ሰው አለማስመረጡ ችግሩ ከምን የመነጨ ነው በሚል ወጣት ካድሬዎቹ ነባሮቹን በጥያቄ ያጣደፉ ሲሆን ነባሮቹም በቂ ምላሽ ለመስጠት ባለመቻላቸው እርስ በርስ በኩርፊያ እየተናጡ እንደሚገኝ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

መስከረም 4 እና 5 ቀን 2005 ዓ.ም የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ባደረገው ስብሰባ ላይ የኦህዴድ ባለስልጣናት የራሳቸውን እጩ ማቅረብ አቅቶዋቸው የሙዋቹ መለስ ዜናዊ ሚስት የህወሀትዋ ስራ አስፈጻሚ አዜብ መስፍን በኩል የኦህዴዱ ባለስልጣን የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትሩ ሱፍያን አህመድ መጠቆሙ ያበሳጫቸው መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ  ኦህዴድን በበላይነት እየመሩ የሚገኙት ትልልቆቹ ባለስልጣናት የራሳቸውን ሰው እጩ አድርገው ያለማቅረባቸው ችግሩ በግልጽ ይነገረን በማለት ወጣት ካድሬዎቹ በብስጭት እየጠየቁ እንደነበርም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በኦህዴድ ውስጥ የተማረ ኃይል እያለ.....በቂ ችሎታ ያላቸው ምሁራኖች እያሉ.....ኦህዴድ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላ መትረፍ የሚችሉ ሰዎች እያሉት የራሱን እጩ መርጦ ለውድድር አለማቅረቡ የበታችነት ስሜት በድርጅቱ ውስጥ ሰርፆ እንዲቀር ሆን ተብሎ የሚሰራ ተንኮል ነው ያሉት እነዚሁ ወጣት የኦህዴድ ከፍተኛ ካድሬዎች ጉዳዩ በአስቸኩዋይ ተመርምሮ መልስ እንዲሰጠን ሲሉም ለኦህዱዱ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳና ለምክትል ሊቀመንበሩ ሙክታር ከድር ጥያቄ ማቅረባቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የኦህዴድ ወጣት ከፍተኛ  ካድሬዎች ያነሱትን ጥያቄ ያደመጡት ሌሎች የወያኔ ባለስልጣናት ለግዜው ጋብ ያለ የሚመስለው በቡድኑ ውስጥ የተከሰተው ትርምስ ሌላ እሳት ተነስቶ እንዳይቀጣጠል በመፍራት አንዱ በልመና ሌላ ግዜ ይሄ የኦነግ አስተሳሰብ ነው በማለት እያስፈራሩዋቸው ጥያቄው ለግዜው ተዳፍኖ እንዲቆይ እያደረጉዋቸው እንደሚገኝም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ለመገንዘብ ተችሎዋል፡፡

በወያኔው ስራ ኢስፈጻሚ ስብሰባ ላይ ምርጫ በተደረገበት ወቅት ብአዴን ሊቀመንበሩን ደመቀ መኮንን......ደኢህዴንም ሊቀመንበሩን ኃይለማርያም ደሳለኝን  እጩ አድርገው  ሲያቀርቡ ኦህዴድ ዝምታን በመምረጡ ከስራ አስፈጻሚዎቹ መሀከል በአዜብ መስፍን በኩል ሱፍያን አህመድን እጩ እንዲሆን ማቅረብዋ አስገራሚ ትርኢት ነበር ተብሎዋል፡፡

በምስጢር ድምጽ ተሰጥቶ ምርጫው ከተጠናቀቀ በሁዋላ በጡረታ የተገለለው አዲሱ ለገሰ በደበዘዘ እና በዳመነ ስሜት ውስጥ በመሆን የምርጫውን ውጤት ሲገልፅ በስብሰባው ላይ ከተገኙት 170

አባላት መሀከል 151 ድምጽ ያገኘው አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ መሆኑን ገልጾ የቀረውን 19 ድምፅ ደግሞ ለሁለት ተካፍለዋል በማለት ነበር ያስታወቀው::በዚህም ግዜ ተሰብሳቢዎቹ ምክትሉ ማን ይሆን በሚል ስሜት በጉጉት ቢጠብቁም ስንት ድምጽ እንዳገኘ ሳይገለጽ በድፍኑ የብአዴኑ ሊቀመንበር ደመቀ መኮንን ምክትል እንደሆነ ተነግሮ ውጤቱ ተቋዋጭቶዋል::

ይህንን ሂደት የሰሙ የኦህዴድ አፍለኛ ካድሬዎች ይሄን ያህል ድራማ ሲሰራባችሁ ምን ስትሰሩ ነበር በማለት ለትላልቆቹ ባለስልጣናት ጥያቄ ቢያቀርቡም የኦህዴድ ስልጣን በፕሬዝዳንቱ የተወከለና የተሰጠን በመሆኑ ውድድር ውስጥ መግባቱ አላስፈላጊ ነው የሚል መልስ ሰጥዋቸዋል ተብሎዋል::

ኦህዴድ ኩማ ደመቅሳ፤ አባዱላ ገመዳ፤ ሶፍያን አህመድ ፤አለማየሁ አቶምሳ ሙክታር ከድር እና የመሳሰሉ እድሜ ጠገብ ሰዎችን ለወያኔ ስራ አስፈጻሚነት አሰልፎ የሚገኝ ቢሆንም በውስጣቸው በተፈጠረ ፍርሀት የተነሳ እንደልባቸው ሀሳባቸውን መግለጽ የማይችሉ በመሆኑ እንኩዋን የድርጅቱን ይቅርና የግል ችግርና ጥያቄያቸውን ደፍረው ለማቅረብ እንደሚቸገሩ ይነገራል::

ወያኔን ከህወሀት ሊቀመንበር ከነበረው መለስ ዜናዊ በስተቀር የመራው አንድም የሌላ አባል ድርጅት ካለመኖሩም በላይ ለ21 ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ ህወሀት ብቻ ሆኖ ቆይቶዋል:: ብአዴንም ቢሆን ለሁለት ግዜ በታምራት ላይኔና በአዲሱ ለገሰ በኩል የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የተሰጠው ይሁን እንጂ ከዚህ ዘልሎ አያውቅም::ኦህዴድ በበኩሉ በኩማ ደመቅሳ እና በአባዱላ ገመዳ የስልጣን እርከን ላይ ተወክሎ ከመቀመጥ ባሻገር ይሄ ነው የተባለ ስልጣን ሳይሰጠው እስከ አሁን ድረስ ይገኛል::

ለዚህም ነው በተለይ የኦህዴድ አፍለኛ ካድሬዎች ለሚያነሱት የህወሀት የበላይነት ሰፍኖዋል የሚል ተደጋጋሚ የስልጣን ይገባናል ጥያቄ መልስ ይሆናል በሚልና ካድሬዎቹን ለማሳመን ሲሉ ስልጣኑን ከህወሀት ነጥቀው ወደ ደኢህዴን ማሽጋገራቸው ተብሎዋል::

በቅርቡ በ151 አባላት ድምጽ አሸንፎዋል ተብሎ በመለስ ምትክ የተሾመው የደቡብ ክልሉ የአረካው ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከወዲሁ ፈታኝ የሆኑ ችግሮችን መጋፈጥ ግድ እንደሚለው የሚገልጹት የፖለቲካ ተንታኞች በተለይ የህወሀት ሰዎችን ለማዘዝ ብዙ ድፍረቱም የሞራል ብቃቱም ስለማይኖረው የተሰጠው ስልጣን የይስሙላ ነው ይላሉ::

ሰሞኑን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የመሪዎች ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ ኒውዮርክ ያቀናው ይሄው የወያኔው አዲሱ መሪ ከአሜሪካው ፕሬዝዳንት እና ከሌሎችም ባለስልጣናት ጋር ሰፊ ውይይት እንደሚያደርግና መመሪያም እንደሚቀበል የጠቆሙት እነዚሁ ተንታኞች የተሰጠውን መመሪያ ሀገር ውስጥ መጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞክር አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ይገልጻሉ::

በመለስ ቀብር ላይ የአሜሪካንን መንግስት በመወከል የተገኘችው ሱዛን ራይስ በሽራተን አዲስ ለረዥም ሰዓት ከኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር ቆይታ ያደረገች ከመሆኑም በተጨማሪ የአሜሪካ መንግስት እና ህዝብ ከጎኑ እንደሆነ የሞራል ድጋፍ እንዳደረገችለት ይነገራል::

በተለይ ከበረሀ የመጡት የህወሀቶችን እና የነበረከትን ሰነሰለት በጣጥሶ በራሱ መንገድ ለመሄድ የማይሞከር ነው የፖለቲከ ታዛቢዎች ከወዲሁ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው ውስጥ ህወሀቶች አብረው ከመጉዋዛቸውና ከመቆጣጠራቸውም በተጨማሪ የመለስን ራዕይ አሳካለሁ እያለ እንዲለፍፍ ማድረጋቸው በእነሱና በእነሱ ትዕዛዝ ብቻ የሚንቀሳቀስ ሮቦት መሆኑን ያሳየ ነው ብለዋል፡፡ በቅርቡም ለአሜሪከ ድምፅ ራዲዮ በሰጠው ቃለ ምልልስ ውስጥ ያሰተላለፈው መልእክትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

እስከ አሁን በታየው አጭር ርቀት ውስጥ ህወሀቶች በተለይም እነ በረከት ስምኦን ኃይለማርያም ደሳለኝ በሙዋቹ መለስ ዜናዊ አምሳያ እንዲፈጠር እየገፉት እና እያስገደዱት ከፍተኛ ጫና እያደረሱበት መሆኑም እየተነገረ ይገኛል፡፡